# ግንቦት 7 እና አዴግ ምንና ምን ናቸው .....!!!

ከታምራት ይገዙ

May 17, 2018



ጋዜጠኛ ፋሲል የኔአለም የጋሼ ሌንጮ ነገር በሚለው መጣጥፉ "አርበኞች ግንቦት 7 እንደ አዴግ አይነቶችን እምነት የማይጣልባቸውን ድርጅቶች እንኳ ለአገር አንድነት ሲባል አቅፎ ለመጓዝ የማይቸግረው ድርጅት መሆኑን አስመስክሯል። አዴግ ለዲሞክራሲና ለአገር አንድነት የሚታገለውን ድርጅት "አላማህን ወድጀዋለሁና አብሬህ ልስራ" ቢል "ተወዳጁ" ድርጅት "እምቢ" ማለት ይቻለዋል? አይመስለኝም። እንዲህ ካለማ ከራሱ አላማ ጋር ተጋጨ ማለት ነው።" እንደ እውነቱ ከሆነ ጋዜጠኛ ፋሲል የኔአለም "እምነት የማይጣልባቸውን ድርጅቶች እንኳ ለአገር አንድነት ሲባል አቅፎ ለመጓዝ የማይቸግረው ድርጅት መሆኑን አስመስክሯል ሲል ይህ ወንድማችን አንድም የግንቦት 7 አባል አሊያም አፍቃሪ መሆኑን ነው የሚያሳብቀው ምክንያቱም ግንቦት ሰባት እንከን የማይወጣለት ድርጅት አድርጎ ለመሳል በማሰቡ::

በሌላ በኩል በኔ እይታ አዴግ ከግንቦት ሰባት ጋር ለመስራት ሃሳብ ያቀረብ አይመስለኝም ምክንያቱም ከዛ ቀደም ብሎ አዴግና ሸንጎ አብረው ሊሰሩ እንደተስማሙ በአዲስ ድምጽ ሬዲዮ ላይ ዶ/ር ቡሻ የሸንጎ አባልና ዶ/ር ዲማ ነጎ ቀርበው ሰፋ ያለ ውይይት አደርገው ነበር:: በኔ ግምት ይህንን የሰሙ የግንቦት ሰባት አመራሮች አገራዊ ንቅናቄ የሚባል ህብረት እንዲፈጠር ለዚህም ታዋቂ ግለሰቦችን ሲፈልጉ ለሸንጎ ጥሩ አመለካከት የሌላቸውን ፕ/ር ጌታቸው በጋሻውና ሻለቃ ዳዊትን ያገኛሉ እነዚህም ታዋቂ ግለሰቦች በስድስት ወር ውስጥ አዋክበው አገራዊ ንቅናቄ የተባለውን በሲያትል ከተማ መሰረቱ:: ፕ/ር ጌታቸውም በእለቱ በአንደበታቸው ሲናገሩ "ይህንን የመሰለ ጠንካራ ህብረት ለመመስረት እኔና ሻለቃ ዳዊት ስድስት ወር ነው የፈጀብን ብለው ነበር":: እኔም የንን ምስረታ ከተመለከትኩ ቦሃላ የተረዳሁት አግላይ ከመሆኑ በላይ ያ ድርጅት እንዲቆቆም የታሰበውአንድም ግንቦት ሰባት በመውደቅ ላይ ስለነበረ ለመታድግ አሊያም የግቦት ሰባት የቀን ቅዥት የነበረውን አውራ ድርጅት ሆኖ የመውጣት አባዜ ለማሳካት መሆኑን በግልጽ ይታወቅ ነበር:: እኔም ያን አይነት የተኮላሸ አካህኣድ በመመልከት በዛ ሰሞን መጣጥፌ

<< የአሜሪካ ሰዎች ኑ ጠላ ቅመሱ

የካናዳ ሰዎች አውሮፓም ያላችሁ ኑ ጠላ ቅመሱ

እንደ መምህሩ አንደ ጌታቸው በጋሻው አንደ ሻለቃ ዳዊት እንድትጠነስሱ>> የሚል ትዝብቴ የያዘ ጹሁፍ አስነብቤ ነበር::

ሰሞኑን ጋዜጠኛ ፋሲል የኔአለም "የጋሼ ሌንጮ ነገር በሚለው መጣጥፉ "አርበኞች ግንቦት 7 እንደ አዴግ አይነቶችን እምነት የማይጣልባቸውን ድርጅቶች እንኳ ለአገር አንድነት ሲባል አቅፎ ለመጓዝ የማይቸግረው ድርጅት መሆኑን አስመስክሯል" ይለናል እንደ ኤውነቱ ከሆነ የጋዜጠኛ ፋሲል የኔአለም ጹሁፍ ፈረንጆች እንደሚሉት"ከነጭ ውሸትነት" ያለፋ አይደለም;;

በኔ እይታ የግንቦት ሰባትን አካሄድን ስመለከትው ከዚህ ቀደም እንደከተብኩት ይህ ግንቦት ሰባት ከተመሰረተ ጀምሮ ህልምና የቀን ቅዠቱ " አውራ ድርጅት" ሆኖ ህወሀት/ኢህኣዴግን ድርጅት ለመተካት ነበር ሲቅበዘበዝ የነበረው እንጂ ኢትዮጵያንና

ህዝቦችን ለመታደግ አልነበረም የሚል እምነት አለኝ:: ይህንን እምነቴን የሚያጠናክርልኝ ግንቦት ሰባት ከተመሰረተ ጀምሮ ሌሎች ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ማለትም በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ላይ ድርድር አያስፈልግም የሚሉ ድርጅቶች አብረን እንስራ ሲሉት ጆሮ ዳባ ልበስ ያለ ድርጅት እንደነበረ እኔ በግሌ በተወሰነ ደረጃ አውቃለው ሌሎችም ያውቃሉ::

በ 2012 በምንርብርት ከተማ ከዶ/ር በርሀኑ ጋር ቁርስ እየበላን ውይይት አድርገን ነበር በዛ ውይይት ላይ ከቀረበው ጠያቂ ለምንድን ነው ግንቦት ሰባት እንደ ታሰበው ወደ ፊት በፍጥነት ሊጎዝ ያልቻለው የሚል ጥያቄ ከአንዲት እህት ቀርቦ ነበር ዶ/ር ብርሃኑም ሲመልሰ " ኤርትራ ውስጥ ያሉ የኦሮሞ ድርጅቶች ለአራት ለአምስት ስለተከፋፈሉ እነርሱን ስናስማማ ነው የከረምነው አሉን:: እኔም በዛላይ ያለኝን ጥያቄ ለመጠየቅ እጄን አነሳው ነገር ግን ዶ/ር ሌላ ቀጠሮ ስለነበራቸው የኔን ጥያቄ ለመቀበል ግዜ አልነበራቸውም:: ከስብሰባ ስንወጣ አንድ ሰው ቀረብ ብሎኝ ለዶ/ር ብርሃኑ የነበረህ ጥያቄ ምን ነበር ብሎ ቢጠይቀኝ የመለስኩለት "በኢትዮጵያዊነት የማያምኑ ድርጅቶችን ለማስታረቅ ከማሰብና ግዜ ከማጥፋት ይልቅ በኢትዮጵያዊ ሉአላዊነት ላይ ምንም ጥያቄ ውስጥ የማይገቡ ድርጅቶች አብራን እንስራ እያሉ እነሱን ወደ ጎን አድርገው ከኢትዮጵያ እንገንጠል ከሚሉ ጋር ለመስራት ግዜ አችውን የምታጠፉት ለምንድን ነው? ግንቦት ሰባት ንቅናቄ እንጂ የተባበሩት መንግስታት ነው ወይ ኢትዮጵያ የምትባል አገር የለችም የሚሉትን ወገኖች ለማስታረቅ ላይ ታች የሚሉት የሚል ነበር ጥያቄዬ አልኩት:: ያም ሰው ጥያቄው ትገቢ ይሁ ወይንም አይሁ በሚገልጽ ምልክት ይመስለኛል አንገቱን ከፍ ዝቅ በማድረግ መለሰልኝ::

እንደ እውነት ከሆነ ግንቦት ሰባት ሲመሰረት እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ድርጅቱን በአባልነት ደረጃ ባይሆንም አቅሜ በሚፈቅደው ሁሉ ደግፌላሁ በመደገፌም የምጸጸትበት ምንም ነገር የለኝም ምክንያቱም ማንኛውም ድርጅት ለአገርና ለህዝብ የሚጠቅም ራይ ሲኖረው መደገፍ ከዛ አይነቱ ራይ ሲያፈነግጥ አለመደገፍ የሁላችንም ምርጫ ይመስለኛል በዚህ መልኩ የግንቦት ሰባትን አካሄድ ከግዜ ወደ ግዜ ስመለከት ቡዙም አብሬ ለመጎዝ ፍላጎቴ እየጠፋ መጣ ምክንያቱም እንደኔ ተከታይ የሆኑትም ሆኑ በአባልነት የተመዘገቡት አብዝኞች በአካባቢዬ ያሉት ግለሰቦች ድርጅቱንም ሆነ መሪዎቹን ወደ ማምለክ ተለወጡ ይህም ለኔ የሚዋጥልኝ ሆኖ አላገኘሁትም ነበር በዚህ መሃል በ 2013 በወረሃ ጥቅምት የግንቦት ሰባት ሊቀመንበር ፕ/ር ብርሀኑ (በወቅቱ ዶ/ር ነብሩ) ከአቶ አበበ ገላው ጋር የኢሳትን አመታዊ በዓል ለማክበር በምኖርብርት ከተማ ተገኝተው ነበር በአሉ ላይ ፕ/ር ብርሀኑ ዛሬ እዚህ የምገኘው ለኢሳት ስለሆነ ስለ ግንቦት ሰባት ጥያቄም ሆነ አስተያየት አልቀበልም ነገር ግን በግንቦት ሰባት ላይ ጥያቄና አስተያየት ያላችሁ በነገው እለት ዳንፎርዝ በሚገኘው ምግብ ቤት ወስጥ ተግኝታችሁ መነጋገር እንችላለኝ አሉ::

እኔም በእለቱ ስብሰባው ላይ ታደምኩ የተለያዩ ጥያቄውችና መልሶች ከተደመጡ ቦሃላ እኔም ተራ ደረሰኝና ተነሳው ጥያቄም ከመጠየቄ በፊት ፕ/ር ብርሀኑ ስብሰባውን ሲከፍቱ እንዲህ በለው ነበር "አሁን እዚህ ያላችሁ ሰዎች ጥያቄ ብቻ አይደለም ስድብም ካላችሁ መሳደብ ትችላላችሁ" ብለው ስለነበር እኔም ይህንን አልኮቸው "በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በአንድ ወቅት የኢትዮጵያ ንጉስ የነበሩ ሰው ሸንጎ ሰብስበው እሲቲ ስደቡኝ ይሉ ነበር ካዛም አንዱ ተነስቶ "ትገርፈኝም እንደሆነ ትገልኝም እንድሆን ከፊትህ ቆሚያላው ያ ለምጣም ሚኒሊክ ቢዬ ሰድቢያለው" ብሎ ተቀመጠ እርሶ ዶ/ር ብርሀኑ ዛሬ ያንን አባባል ነው ያስታወሱኝ ካልኩኝ ቦሃላ ጥያቄዬን እንዲህ በማለት በአስታተያየት ጀመርኩ::

ዶ/ር ብርሃኑ የደርጅቶት አባልና ደጋፊ የሆኑ ሰዎች ድርጅቱንና እርሶን ከመደገፍና ከማገዝ ባለፈ መልኩ እርሶን; ድርጅቶትን ግንቦት ሰባትና እንዲሁም ሚዲያን (ኢሳትን) ማምለክ ጀምረዋል ብዬ ወደ ግንቦት ሰባትና የሻቢያን ግንኙነት በተመለከተ ገና ከመጀመሬ በዶ/ር ብርሃኑ በግራ በኩል ተቀምጣ የነበረች እህት ስሜን በመጥራት ተቀመጥ ተቀመጥ አለች አሶን ተከትሎ ሌላው ወንድም ከወደ በሩ ሆኖ ተቀመጥ ተቀመጥ አለ እኔም የእነዚህ ሁለት ሰዎች ጫጫታቸውን ከስጨረሱኩ ቦሃላ "ዶ/ር ብርሃኑ እርሶ ጥያቄ አይደለም ስድብም ካላችሁ ተሳደቡ ለማስተናገድ ዝግጁ ነኝ ብለው እድሉን ቢሰጡኝ እነዚህ ሁለት ሰዎች የሚሉትን ይሰማሉ? እነዚህ ሰዎች የእርሶና የደርጅቶት ደጋፊዎች ሳይሆኑ የርሶና የድርጅቶት አሚላኪዋች ነቸው ይህንን በግዜ ካላስወገዱ የኾላ ኾላ ለርሶም ሆነ ለድርጅቶት ዋጋ የለውም ምክንያቱን "አምልኮ ለፈጣሪ" እንጂ ለግለሰብ; ለድርጅትና ለሚዲያ አይደለም አልኮቸው :: ዶ/ር ብርሃኑም ሲመልሱ አንተ እንዳሰብከው አምላኪዎች ሳይሆኑ ካለው ግዜ አንጻር ነው ብለው መለሱ እኔም የተሰማኝን ተናገርኩ እርሳቸውም መልሳቸውን ተናገሩ::

በነገራችን ላይ ያን ግዜ ያዙኝ ልቀቁኝ ከሚሉት አምላኪዎች ግማሾቹ ለግንቦት ሰባት ስብሰባ ኤርትራ ደርሰው ከመጡ ቦሃላ በኤርትራ በኩል የሚደረገው ትግልም ሆነ ጋዜጠኛ መሳይ መኮንንና ጋዜጠኛ ፋሲል የኔአለም ኤርትራ ድረስ ተጉዘው ያቀናበሩት ቅንብር ከጋዜጠኛ ስነ ምግባር የወጣና የልማታዊ ጋዜጠኛ ያዘጋጀው መሆኑን በዓይናቸው አይተው ስለተረዱት አባቶቻቻን የሚሉትን አባባል "ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል" የሚለውን በማስታወስ ግንቦት ሰባትን አይንህን ለአፈር ብለው

ቤታቸው መቀመጥን ከመረጡ ሰንበት በት ብለዋል::

ወደ ጋዜጠኛ ፋሲል የኔአለም የጋሼ ሌንጮ ነገር ወደሚለው መጣጥፉ ስመለስ ጋዜጠኛ ፋሲል የኔአለም ሊነግረን እንደሚያስበው ሳይሆን ግንቦት ሰባት የተጎዘው ጉዞ ከፈረሱ ጋሪው ቀደሞ በሚዲያ አጃቢነት እንጂ በትግሉ ውስጥ እንደ መቆየቱ ምንም የስመዘገበው እሚንት የሆነ ነገር አይታይም:: ይህንን ከተመለከትኩ ቦሃላ በምኖርበት ከተማ ላሉ የግንቦት ሰባት አባል ለሆነና ለግንቦት ሰባት ጥሩ አመለካከት አላቸው ከምላቸው ወንድሞች የተለያየ ውይይት ሳደርግ የሚሰማኝን ከመናገር አልቆጠብም ነበር:: ለምሳሌ ሁላችንም እንደምናውቀው የግንቦት ሰባት ከፍተኛ አመራሮች በአንድ ወቅት ትግሉን ለመምራት ብለው ጠቅልለው ኤርትራ ገብተው ነበር አብረው እንደገቡ ሁሉ እብረው ወጥተው እንደነበር አይዘነጋም ይህንን በተመለከተ ከአንድ ወንድም ጋር ስወያይ "ኤርትራ የገቡት የግንቦት ሰባት አመራሮች ይህው ሁሉንም ነገር አይተው ተመልሰዋል ሁሉም እንደሚገነዘበው በኤርትራ በኩል የተኼደው ጉዞ ጥቅሙ ስላልታየ ለምን አሁን የግንቦት ሰባት አመራሮች ለግዜው የትጥቅ ትግሉን ሙሉ በሙሉ ትተን (Suspended ) እድርገን ያለ የሌለ ሀይላችንን ሰላማዊ ትግሉ ላይ እንድናውል ግዜው የግድ ስለሚል ብለው ለአባላቶቻቸው ለውይይት አያቀርቡም ብለው ይህ ወንድሜ የሰጠኝ መልስ አንተ ሞኝ ነህ እንዴ" ግንቦት ሰባት ይህን የሚያደርገው ኢህአፓ ወይንስ ሸንጎ ደስ እንዲለው ነው የሚል መልስ ነበር የሰጠኝ" እኔም ስመልስለት ላካ ትግሉ ማን ደስ ይለዋል ማን ይከፋዋል ነው እንጂ የአገርና የህዝብ ጉዳት አይደለም የሚያሳስባችሁ በማለት ነበር የመለስኩለት::

የኦዴግ አመራሮች አገር ቤት እንደሚገቡ ስሰማ ይኸው ወዳጄ ጋ ስልክ ደውዬ ሳወራው ይህንን ጨዋታችንን አስታወስኩት እርሱም ስመልስ "አዎ ብለኸኝ ነበር ነገር ግን ዶ/ር አብይ ለስልጣን ይበቃል ብሎ ከሶስት ወር በፊት ያሰበ ማን አለ አለኝ" እኔም ስመልስለት የድርጅት መሪ የሚመጣውን ሶስት ወር ሳይሆን ፎር ካስት ማደረግ ያለበት ከዓመትና ከሁለት ዓመት ቦሃላ ምን ይመጣል ብሎ ካላሰበ ከኔ ከተራው ግለሰብ በምን ተሻለ ስለው መልስ አልነበረውም::

በአጠቃላይ በአሁኑ ዘመን የሚደረገውን ሁሉ በቀላሉ ለሚከታተልና ለሚያውቅ ሰው ጋዜጠኛ ፋሲል የኔአለም ግንቦት ሰባትን ትክክለኛ መንግድ የተጎዘና "እንደ ኦዴግ አይነቶችን እምነት የማይጣልባቸውን ድርጅቶች እንኳ ለአገር አንድነት ሲባል አቅፎ ለመጓዝ የማይቸግረው ድርጅት ነው ሊለን ሞሞከሩ የተሳሳት ሙገሳ ለግንቦት ሰባት ለመለገስ ማሰቡን ነው የሚያሳየው ይህም በኔ እይታ ስህተት ከመሆኑ ባሻገር ድርጅቱ ከድጡ ወደ ማጡ እንደመከተትና ከስህተቱንም እንዳያርም ማድረግ ነው ብል ማጋነን አይሆንብኝም::

በመጨረሻም ለግንቦት ሰባት አመራሮችና አባላቶች እንዲሁም ለድርጅቱ ቅናዊነት ላላቸው ሰዎች ያለኝ መልእክት ፖለቲካ እንደ ሀይማኖት "ዶግማ " አይደለም ስለሆነም እንደ ግዜውና እንደ አካባቢው ሁኔታ የሚለወጥና የሚሻሻል ስለሆነ በዓሁኑ ሰዓት በዓለም ያሉ መሪዎች በተለይ ምዕራብያውያን የአንድ ሀገር ህዝቦች እርስ ብረሳቸው ተዋግተው የመንግስት ለውጥ እንዲመጣ የሚፈልጉ እይደሉም ምክንያቱም በኔ እይታ ጦሱም ለነሱ እንደሚደርስ ያውቃሉና:: ስለሆነም ግንቦት ሰባት አመራሮች በመሳሪያ ትግል መንግስት መለወጥ የሚሉትን ሃሳብ ቀይረው ሙሉ በሙሉ በሰላማዊ ትግል ለመታገል ለአባላቶቻቸውም ሆነ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ይፋዊ የሆነ መግለጫ የማውጫ ሰዓታቸው አሁን ይመስለኛል::

እርግጥ ነው የድርጅት አባላቶችም ሆኑ ደጋፊዎች በሁኔታው ላይደሰቱ ይችላሉ አማራሮቹንም በጥያቄ ሊያጣድፉ ይችላሉ በኔ እምነት መሪ ማለት ተከታዩን ማሳመን የሚችል ሰው ነው:: ይህንን ማድረግ የማይችል መሪ በፊትም የመሪነት ችሎታው አጠያያቂ ነበር ማለት ነው እያልኩ የዛሬን ጹሁፌን ልቆጭ::

አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ይፈቱ!

አምላክ አገራችንን ኢትዮጵያን በምህረቱ ይጎብኝልን!!